# Learning by Ear 2013

**መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ**

EPISODE TWENTY-ONE: **መጥፎ ዜና**

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: አቶ ደንበል , KADU AND ብሩክ AT CHECKPOINT**

- **OFFICER (M, 40)**
- **አቶ ደንበል (M, 45)**
- **ብሩክ (M, 8)**

**SCENE 2: ምህረት AND አቶ ሙላቱ AT HOME**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**

**SCENE 3: አቶ ካሳሁን MAKES A SURPRISE VISIT TO ዳንኤል 'S SCHOOL**

- **በለጠ (M, 15)**
- **ዳንኤል (M, 16)**
- **አቶ ካሳሁን (M, 55)**

1. **<u>INTRO – NARRATOR:</u>**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ድራማ ነዉ። እስቲ ያለፈውን መለስ ብለን እናስታውስ።

ምህረት ከክፍል ጓደኛዋ ንጉሴ ደብዳቤ ደርሷታል። ንጉሴ ወላጆቹ በቅርቡ ተዘርፈው ስለነበር የጠረጠሩት የቀድሞ የጥበቃ ሰራተኛቸው የምህረት አባትን ፤አቶ ሙላቱን ነው።

2. **SFX: PAPER BEING UNFOLDED (EP 20, LINE 96)**

3. **ምህረት :** “ምን እየቀለድክ ነው? ንጉሴ፤ ምን እያልክ ነው? በፍፁም ይህ እውነት ሊሆን አይችልም።

ምህረት በጊዜ አባቷን ስለመጠርጠራቸው ታስጠነቅቃቸው ይሆን? አቶ ሙላቱ በርግጥ ከዝርፊያው በስተጀርባ ይሆኑ እንዴ? ካለፉት ጥቂት ወራት አንስቶ ነገሮች ሁሉ ተቀያይረዋ።አቶ ሙላቱ ብዙ ይጠጣሉ። የጥበቃ ስራቸውን ትተዋል። ባለቤታቸው ጥለዋቸው ሄደዋል። ይህም አልበቃ ብሎ እህታቸው ለምለም ጋ ላቦሪያ እንዲኖሩ የላኳቸው መንታ ልጆች ጠፍተዋል። ቅዱስ እና ብሩክ ጎዳና ላይ ሲለምኑ ባጋጣሚ ያገኟቸው አንድ ሹፌርም ሊረዷቸው ተስማምተው ጉዞ መጀመራቸውን ባለፈው ክፍል ሰምተናል።:

4. **አቶ ደንበል (EP 20, LINE 55):** “በዚህ መኪና በፍጥነት ልነዳ አልችልም። ዕድለኞች ከሆንን ነገ እንደርሳለን። **(+57)** “በነገራችን ላይ ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ አባታችን ነው ነው የምትሉት።!”

5. **ብሩክ & KADU (62):** “እሺ.”

እስኪ« መጥፎ ዜና» የተሰኘው የዛሬ 21ኛ ክፍል ታሪክ ወዴት እንደሚያመራ አብረን እንከታተል። አቶ ደንበል እና ልጆቹ አንድ የፖሊስ ፍተሻ ኬላ ላይ ደርሰዋል። …

**<u>SCENE 1: አቶ ደንበል , KADU AND ብሩክ AT CHECKPOINT</u>**

6. **RURAL DAYTIME ATMO**

7. **SFX: TRUCK SLOWLY COMING TO A STOP**

**8. SFX: RADIO ON**

**9. OFFICER:** **(ordering from outside through open truck window)** መኪና ውስጥ ያላችሁ በሙሉ ውረዱ። ሹፌር መኪናውን እንድንፈትሽ በሩን ክፈትልን!

**10.** አቶ ደንበል: እሺ ወታደር፤ አንድ ጊዜ ልጆቼን ልቀስቅሳቸው። **(whispers in truck)** ብሩክ ! ቅዱስ! ልጆች ተነሱ። ፍተሻ ኬላው ላይ ደርሰናል። ከመኪና መውረድ አለብን።

**11. SFX: SNORING FROM TWO YOUNG BOYS**

**12.** አቶ ደንበል : በጣም ይቅርታ ወታደር። ሁለቱም ልጆቼ እንቅልፍ ላይ ናቸው። የተጓዝነው ረዥም መንገድ ነው።

**13. OFFICER:** **(curious)** ሁለት ልጆችዎን ይዘዋል? ላያቸው እፈልጋለሁ። እያንዳንዱን ነገር መፈተሽ እፈልጋለሁ።

**14.** አቶ ደንበል: **(with confidence)** አላይ መተኛው ላይ ናቸው። መጥተው ሊያዩዋቸው ይችላሉ። ግን ግዴታ ባትሪ መጠቀም አለብዎ? ባይቀሰቅሷቸው ደስ ይለኛል። ፀጥታ እና ሰላሙ ጥሩ ነው። መቼም ያውቃሉ ልጆች መንገድ ላይ ሲሆኑ እንዴት እንደሚረብሹ።

**15. OFFICER**: አዎን የሚሉት ይገባኛል። ወዴት እየሄዱ ነው?

**16.** አቶ ደንበል : ወደ ታንዲካ በመመለስ ላይ ነኝ። … ላቦሪያ የማደርሰው እቃ ነበረኝ። እና ልጆቹ አገሩን ቢያዩት ይወዱታል ብዬ ይዣቸው መጥቼ ነው። በጣም ነው የወደዱት።

**KW BEGIN**

**17. OFFICER**: **(friendly voice)** ለመገመት አያዳግተኝም። ይገባኛል። አዩ እኔም አንድ ወንድ ልጅ አለኝ።...

**18.** አቶ ደንበል : እውነት? የስንት አመት።

**19. OFFICER**: አምስት አመቱ ነው። ሌላ ደግሞ አንዲት --

**20. KADU: (dreaming; faintly, from inside truck)** አባክህ አባክህ ተወኝ። ... ደክሞኛል። ...አትምታኝ...

**21. OFFICER**: የሆነ ነገር ሰማሁ ልበል? ይሄ ድምፅ የመጣው ከመኪናዎ ውስጥ ነው?

**22.** አቶ ደንበል : ሬዲዮ ነው። አዩ ስነዳ እንቅልፍ እንዳይወስደኝ ከፍቼው ነበር።

**23. OFFICER**: ለመሆኑ ምንድን ነው የጫንከው? የኮንትሮባንድ እቃ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

**24.** አቶ ደንበል : እረ አይደለም። በፍፁም አላደርገውም። ትንሽ ኩንታል በቆሎ፣ ሩዝ ፣ ባቄላ የመሳሰሉትን ነው የጫንኩት። የጉዞ ማስረጃዎቼን ሊመለከቱ ይችላሉ።

**KW END**

**25. OFFICER**: አስፈላጊ አይደለም ይተውት። ታማኝ ሰው ይመስላሉ። መልካም ጉዞ ይሁንልዎ። ልጆቹ ሲነቁ ሰላም ይበሉልኝ።

**26.** አቶ ደንበል : **(politely)** በሚገባ በሚገባ። አመሰግናለሁ ጌታዬ።

**27. SFX: STEPS OFFICER LEAVE**

**28.** አቶ ደንበል**: (takes deep breath)** ለጥቂት ተረፍኩኝ!

**29.** ብሩክ**: (sleepy voice)** ሽንቴን መሽናት እፈልጋለሁ!

**30.** አቶ ደንበል : አሁን አልችልም ብሩክ ! ከዚህ ቦታ በፍጥነት ነድቼ መውጣት አለብኝ። ማቆም አልችልም። በኋላ ግን ቃል እገባልሀለሁ።

**31. SFX: TRUCK ENGINE STARTS, TRUCK DRIVES OFF**

**32. MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 2: ምህረት AND አቶ ሙላቱ AT HOME</u>

**33. SFX: EVENING ATMO AT** አቶ ሙላቱ

**34.** አቶ ሙላቱ **:** **(angry)** ምህረት ! ምህረት !

**35. SFX:** ምህረት **ARRIVES**

**36.** ምህረት : አለሁ። አቤት?

**37.** አቶ ሙላቱ : ምህረት ፤ ቆሻሻውን ማቃጠል ነበረብሽ። ግን ምንም ሳትሰሪ መሸ።

**38.** ምህረት **:** ይቅርታ አባዬ። የቤት ስራ እየሰራሁ ነበር።

**39.** አቶ ሙላቱ **:** የቤት ስራ። ኤዲያ! ይህ ነው የቤት ስራሽ። ቤትሽ እዚህ ነው።

**40.** ምህረት **:** **(shyly)** አውቃለሁ አባዬ።

**(short pause)**

**41.** አቶ ሙላቱ **:** ለምንድን ነው እንደዚህ በሚገርም አስተያየት የምትመለከቺኝ?

**42.** ምህረት **:** እ? እኔ?

**43.** አቶ ሙላቱ **:** አዎ! አንቺ! ይህን አመለካከት አውቀዋለሁ። አሳዛኝ እና የጥርጣሬ ፊት። አዎ! ይህን የወረሽው ከእናትሽ ነው። የሆነውን አሁኑኑ ንገሪኝ። አልያ ይህንን አስተያየትሽን አቁሚ።

**44.** ምህረት : አባዬ ዛሬ ትምህርት ቤት ሳለሁ… ቆየኝ. **(fumbles a paper out of her pocket)** አንድ ሰው ይህንን ማስታወሻ ሰጠኝ። የሚለውም አንተ በዘረፋ ወንጀል ውስጥ እንዳለህበት ነው።…?

**45.** አቶ ሙላቱ : **(furious)** ማን አባቱ ነው ደግሞ እንዲህ የሚለው…? **(mumbling something unintelligible)**

**46. SFX: TAKES THE PAPER, TEARS IT INTO PIECES**

**47.** አቶ ሙላቱ : **(shocked)** እቺን ይወዳል ሙላቱ፤ ስታይኝ ቀማኛ እመስላለሁ? ማነው ይህንን የነገረሽ?

**48.** ምህረት : ማስታወሻውን የሰጠኝ ንጉሴ ጃለታ ነው። የኛ ክፍል ተማሪ ነው። ወላጆቹ ባለፈው ሳምንት ተዘርፈው ነበር። እና አንተ በነገሩ እንዳለህበት ነው የሚጠረጥሩት። ምክንያቱም አንተ እነሱ ጋ በዘበኝነት ትሰራ ስለነበር እና በድንገት ስራህን ስላቆምክ ነው።

**49.** አቶ ሙላቱ : **(defensive)** እና ያቆምኩ እንደሆንስ? 10 አመት ሙሉ በዘበኝነት የሰራ ሰው ስራውን ቢያቆም ወንጀል ነው? **(stresses, with bitterness) –** 10 አመት ሙሉ ጠብ ለማይል ገንዘብ። እና የቀድሞ ቀጣሪዎችህ በሌብነት እየጠረጠሩህ ነው ነው የምትይኝ? ዳሩ ግን አስር አመት ሙሉ ንብረታቸውን እየጠበኩላቸው ነበር። መቼም የሰው ነገር።

**50.** ምህረት : አውቃለሁ አባዬ። ፖሊስ ፣ አቶ ጃለታና ባለቤታቸው ግን አያምኑህ ይሆናል። ፖሊሶች በቅርቡ ሊመጡ ስለሚችሉ ምናልባት … ብትሄድ ሳይሻል አይቀርም።

**51.** አቶ ሙላቱ : ምህረት ምን እያልሽ ነው? መሄጃ ምንም ቦታ የለኝም።…

**52.** ምህረት : ወደ እማዬ ወላጆች ጋ መሄድ ትችላለህ። ገጠር ትሄዳለህ ብሎ ማንም ሰው አያስብም።

**KW BEGIN**

**53.** አቶ ሙላቱ : በጭራሽ አያቶችሽ ጋ አልሄድም። እናትሽ ከኛ ወደሸሸችበት እንዴት አድርጌ ነው መጠልያ የምፈልገው? እሷ ከፈለገች ልታደርግ ትችላለች። እኔ ግን አላደርገውም። በዛ ላይ የገጠር ኑሮ?!

**54.** ምህረት : አባዬ ይህንን ከእማዬ ጋ ሆነህ ልትወያይበት ትችላለህ። አሁን ግን ያለን ጊዜ በጣም አጭር ነው። እድሜ ለንጉሴ በጊዜ አስጠንቅቆናል።ግን ከአሁን በኋላ በማንኛውም ሰዓት ፖሊስ በር ሊያንኳኳ ይችላል።

**KW END**

**55.** አቶ ሙላቱ: **(worried)** ግን እኮ ለአውቶቢስ ቲኬት መግዣ እንኳን የሚሆን ሳንቲም የለኝም። ...እንዴት ብዬ ነው የምጓዘው?

**56.** ምህረት : እኔ እሰጥሀለሁ።

**57.** አቶ ሙላቱ: **(concerned)** ምህረት ! ገንዘቡን ከየት ነው ያመጣሽው? ፍቅረኛ አለሽ ልበል? ወይንስ ሀብታም ሽማግሌ ናቸው የሰጡሽ?

**58.** ምህረት : ይሄውልህ አባዬ ስለ እኔ አታስብ። ለራሴ መሆን አያቅተኝም።

**59. SFX: KNOCK AT THE DOOR**

**60.** አቶ ሙላቱ: **(scared stiff)** ፖሊሶቹ ናቸው ምህረት ... ምን ባደርግ ይሻላል? ንገሪኝ።

**61.** ምህረት : ቆይ መጀመሪያ ላጣራ።

**62. SFX: FOOTSTEPS WALKING ACROSS FLOOR**

**63.** ምህረት : ማን ነው?

**64.** ትዕግስት : **(through the door)** ምህረት ከፈቺው ትዕግስት ነኝ።

**65.** አቶ ሙላቱ : **(still scared)** ምህረት በሩን እንዳትከፍቺ ሊያታልሉን ይሆናል።

**66.** ምህረት: **(whispers)** አባዬ! ትዕግስት ጓደኛዬ ናት። አንተ ከቤት ወጥተህ ሳለህ መታ ነበር።

**67. SFX: DOOR UNLOCKED**

**68.** ምህረት : ታድያስ ትዕግስት !

**69.** ትዕግስት : **(worried)** ታድያስ፤ ስለረበሸኳችሁ በጣም ይቅርታ ጋሽ ሙላቱ ። ግን ምህረትን አንዴ ላናግራት ፈልጌ ነበር።

**70.** ምህረት : እሺ ግቢ ወደ ውስጥ…

**71. SFX: DOOR BEING OPENED**

**72. SFX: FOOTSTEPS WALKING IN**

**73.** ምህረት : ተቀመጭ። አባቴን ተዋወቂው ትዕግስት ።

**74.** አቶ ሙላቱ : እንደምን አለሽ ትዕግስት ። ምህረት … እክፍሌ ውስጥ ሆኜ እቃዬን ላዘጋጅ።

**75.** ትዕግስት : በዚህ አጋጣሚ እንk/ንም ተዋወቅን ጋሽ ሙላቱ ።

**76. SFX: FOOTSTEPS LEAVING ROOM**

**77.** ትዕግስት **(to** ምህረት**)** እሺ - ወዴት ልትሄጂ ነው?

**78. SFX: CHAIRS PULLED OUT**

**79.** ምህረት : እኔ? እኔ አይደለሁም አባዬ ነው የሚሄደው።…በይ እሺ ንገሪኝ። እስከ ነገ ድረስ አላስጠብቅ ያለሽ ምን ገጥሞሽ ነው?

**80.** ትዕግስት : **(very concerned, low voice)** ምህረት እንደሚመስለኝ፤ የአባላዘር ይዞኛል።

**81.** ምህረት: ምንድን ነው የአባላዛዘር? በጣም የተጨነቅሽ ትመስያለሽ ትዕግስት ።

**82.** ትዕግስት: አባላዘር አታውቂም? በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ የሚተላለፍ በሽታ ነው።

**83.** ምህረት: **(shocked)** ወየው ጉድ ትዕግስት ፧ርግጠኛ ነሽ? ምናልባት የHIV ቫይረስ ማለትሽ ነው?

**84.** ትዕግስት: አይ አይደለም። አንቺ ደግሞ በጣም አበዛሽው። አባላዘር ነው ያልኩሽ።...

**85.** ምህረት : እንዴት ሊይዝሽ ቻለ? ስለመያዝሽስ በምን አወቅሽ?

**86.** ትዕግስት : ከታክሲ ረዳቱ ነው የያዘኝ ብዬ እገምታለሁ። የህመሙን ምልዕክቶች አውቃቸዋለሁ። ሲያመኝ የመጀመሪያ ጊዜዬ አይደለም።

**87.** ምህረት: **(a bit surprised by the response)** ትዕግስት – በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ከዚህ ቀደም ይዞኝ ያውቃል ነው የምትይኝ? መቼ? እንዴት ስለዚህ ከዚህ ቀደም ሳትነግሪኝ ቀረሽ?

**88.** ትዕግስት : **(sarcastic)** እኔ ባክሽ ስለእዛማውራት ደስ አይለኝም። ለማንኛውም ለህክምና ስል ለሚመጡት ጥቂት ቀናት ት/ቤት እንደማልመጣ ልነግርሽ ነው አሁን የመጣሁት።

**89.** ምህረት : ትዕግስት በጣም ነው ያስደነገጥሽኝ። ለመሆኑ በጣም አደገኛ ነው?

**90.** ትዕግስት : ሁሉም አይነት የአባላዘር በሽታዎች በተወሰነ መልኩ አደገኛ ናቸው። ቢያንስ ይሄንን ነው ሀኪም የነገረኝ። ሀኪም ቤት ሄጄ ነበር ቅድም። ሀኪሙ መጥፎ ሁኔታ ላይ እንዳልሆንኩ ግን እንድጠነቀቅ ነግሮኛል።

**91.** ምህረት : ግን ... ስሜቱ ... እንዴት ነው?

**92.** ትዕግስት : በጣም ያሳክክሻል። ከዛ ደግሞ ሽንት መሸናት እምቢ ይልሻል።....

**93.** ምህረት : ወይጉድ እና ወላጆችሽ ምን አሉሽ?

**94.** ትዕግስት: **(surprised)** አብደሻል እንዴ? እንዴት ብዬ ነው ስለዚህ ለወላጆቼ የምነግራቸው?

**95.** ምህረት: **(realizes)** ወይኔ እና እኔንም ይዞኝ ይሆን እንዴ?

**96.** ትዕግስት : **(puzzled)** አይዞሽ አንቺ ምንም አትሆኝም። አትጨነቂ አይገለኝም።

**97.** ምህረት : ምን መሰለሽ! ትዕግስት ፤ ነገሩ አልገባሽም። ... ዳንኤል እና እኔ ... ገባሽ... **(under her breath)** ከእንግዲህ ድንግል አይደለሁም።

**98.** ትዕግስት: **(surprised - whispering)** ምን? ምህረት ! አንቺ እና ዳንኤል ? እና... ተሰበረ?

**99. SFX: FOOTSTEPS -** አቶ ሙላቱ **APPROACHING**

**100.** አቶ ሙላቱ : **(clears throat)** ምህረት ...መሄዴ ነው።

**101. SFX: MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3:** አቶ ካሳሁን **MAKES A SURPRISE VISIT**

**100. SFX: BASKETBALL BEING DRIBBLED, SHOTS TAKEN**

**101. SFX: TWO PEOPLE RUNNING**

**102.** በለጠ : **(celebrates)** ዋው! ምን አይነት ምት ነው በለጠ ። 5 ለ 4። አሳየው ላለየው አንተ አደገኛ ልጅ።

**103. SFX:** ዳንኤል **JUMPS**

**104. SFX:** ዳንኤል **SCORES**

**105.** ዳንኤል: **(takes a deep breath)** እረ ረ! 5 - እኩል! በቃ! አሁን ትንሽ ልረፍ።

**KW BEGIN**

**106.** በለጠ: **(sarcastic)** ሃ ሃ ሃ ! ጉልበት የለህም እንዴ ዳኒ!

**107.** ዳንኤል : በል ዝም በል።እኩል ለኩል ስትወጣ ይህ የመጀመሪያ ጊዜህ ነው። ጉራህን አትንፋ።

**KW END**

**108. SFX: CLAPPING OF HANDS**

**109.** አቶ ካሳሁን : **(far off, proudly)** ይሄ ነው የኔ ልጅ። ምን ያህል ጠንካራ እንደሆንክ አሳያቸው።

**110. SFX: FOOTSTEPS APPROACHING**

**111.** ዳንኤል: **(shouting, startled)** አባዬ እዚህ ምን ታደርጋለህ?

**112.** በለጠ : እንዴ ዳኒ - አባትህ ናቸው እንዴ? ትንሽ… **(whispers)** ቋ ያሉ ይመስላሉ…

**113.** ዳንኤል : አባዬ መቼ ነው የመጣኸው? በፍፁም ትመጣለህ ብዬ አልገመትኩም ነበር።

**114. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**115.** አቶ ካሳሁን : ሳታስበኝ ከች ልበል ብዬ ነው። ርዕሰ መምህርቷ እንኳን የእኔን እዚህ መሆን አታውቅም። ዘበኛውን በደንብ አድርጌ አዋራሁት እና፤ ስልቴን ታውቀው የለ? እናም ግባ አለኝ። እናንተ ሁለታችሁ በደንብ እንደምትተዋወቁ ነገረኝ።

**116.** ዳንኤል : አባዬ - ይህ ነው በለጠ ።

**117.** በለጠ : እንደምን አሉ የዳንኤል አባት። ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል አቶ ካ--

**118.** አቶ ካሳሁን: **(interrupts him)** ስራ አስኪያጅ አቶ ካሳሁን ።የካሳሁን ድርጅቶች ስራ አስኪያጅ። ዳንኤል ስለእኔ ማንነት አልነገረህም እንዴ?

**119.** በለጠ : **(formally)** ኧረ። እንደሚመስለኝ አረስቼው ነው። እንኳን ደህና መጡ አቶ ስራ አስኪያጅ ካሳሁን። አሁን ሄጄ ትንሽ ላጥና። እስከ በኋላ ዳንኤል።

**120. SFX: FOOTSTEPS LEAVE**

**121.** አቶ ካሳሁን : ጥሩ! እሺ... ይኼው መጥቻለሁ። አዲሱ ትምህርት ቤትህን ልይ ብዬ እኮ ነው።....በዛ ላይ እንዲህ አልማዝን ስላስረሳችህ እና በፍቅር ስላሳበደችህ አዲሷ ፍቅረኛህ ልጠይቅህ ነው።

**122.** ዳንኤል : እረ - ምን እያልክ ነው አባዬ?

**123. MUSIC INTERLUDE**

**124. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

ዳንኤል ተደናግጦ እና ግራተጋብቶ ላቡ ከካናቴራው ጠብ ሲል እኛም የእዚኛውን ክፍል እናበቃለን። ከፖሊስ ለማምለጥ በሙከራ ላይ ያሉት አቶ ሙላቱ ምን ይገጥማቸው ይሆን? የትዕግስትን መጥፎ ዜና ከሰማች በኋላ ምህረት ተጨንቃለች። ከዳንኤል ጋ የነበራትም የግብረ ስጋ ግንኙነት እያሳሰባት ነው። ፍርሃቷ ወደ እውነት ይቀየር ይሆን? የሚቀጥለው ክፍል እንዳያመልጣችሁ። ይህንን ክፍል ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ ጤና ይስጥልን።